# በአቶ ሽባባው ድብ አንበሳ ሆቴል ተሰቅሎ የነበረው የግንቦት 7 ማስታወቂያ በወጣቱ ግፊት ተነስቷል።

September 12, 2018

ዛሬም ለምን ብላችሁ ጠይቁ! (ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው )

በ2008 ዓም ባህርዳር ላይ የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ይታሰራሉ። ዛሬ ሁሉም "ሰላማዊ ትግል ውስጤ ነው" ሲል፣ ሰላማዊ ትግል ስድብ ሆኖ ነበር፣ ከገዳዮች ጋር ፊት ለፊት የሚጋፈጡ ወጣቶች ፈሪ ተብለው ተሰድበዋል። ሰላማዊ ትግል አያስፈልግም ተብሎ ተዘፍኖበታል። ዘመቻ ተደርጎበታል!

በ2008 ዓም የአማራ ሕዝብም ነፍጥ ያነሳበት ጊዜ ነበር። ሕዝቡም በሰላማዊ ትግል ከሚታገሉት ይልቅ ነፍጥ ያነሱት ይደርሱልናል ብሎ አምኖ ነበር። የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ባህርዳር ላይ ታስረው የገጠማቸው ተመሳሳይ ነበር። የታሰሩበት ጣቢያ ፖሊሶች ሳይቀሩ "ተስፋችን ግንቦት 7 ነው" ብለው በድፍረት ነግረዋቸው ነበር።

ሀምሌ 5፣ ነሃሴ 1 /2008 ዓም በኋላ ሕዝብ የታጠቀ አካል ይደርስልኛል ብሎ ያምን ነበት። ግንቦት 7 ተስፋ በተጣለበት መልኩ ለሕዝብ አልደረሰም። እንዲያውም ትዝብት ውስጥ ገባ። ትችት የማይቀበሉ አባላትና አመራሮቹ መበርከት ፕሮፖጋንዳ ላይ ብቻ የተጠመደ ድርጅት ሆነ። የሕዝብ ድጋፍ ሳያጣ መታመን አቃተው። ፕሮፖጋንዳ አበዛ። የገበሬውን ትግል የእኔ ነው አለ። በ"ሰሜን እዝ" የተሰሩ ዜናዎችን ብንመረምራቸው ብዙ አስቂኝ ነገር እናገኛለን! ብዙውን ታዝበን አልፈናል። ሕዝብ ግን እምነት ሲያጣ፣ ሲገምት፣ ሌላም ሌላም ነገር ሲያይና ሲሰማ አለመደገፍ ብቻ አይደለም ይጠላል።

የትኛውም አካል በአመለካከቱ መመዘን አለበት ብየ አምናለሁ። ነገር ግን ሕዝብ ለምን እንዲህ ጠላኝ ብሎ መጠየቅ የድርጅቱ ጉዳይ መሆን አለበት።



ትችትን በቀናነት መስማት፣ ሰምቶ ማስተካከል ትልቅነት ነው። የተቸን ሁሉ ጠላት ማድረግ መጨረሻው መጠላት ነው። ትናንት የግንቦት 7 ማስታወቂያ በአቶ ሽባባው ሆቴል ተሰቅሎ ነበር። ዛሬ በወጣቱ ግፊት ተነስቷል ተብሏል።

ግንቦት 7 ገና ወደ ሀገር ቤት መግባቱ ነው። እስከዛሬ ትችት ሲቀርብ ከገዥዎቹ ካድሬዎች ያልተለዩ ጭፍን ደጋፊዎቹ ዘለፋና ዘመቻ እንጅ ለድርጅት ግብዓት አያደርጉትም። ዛሬ ወጣቱ "አንያችሁ" እስከማለት ደርሷል። ግንቦት 7 ትልልቅ ፖለቲከኞች ያሉት ድርጅት ነበር። ማንም ገብቶ ሲያቦካ፣ ሕዝብ ቅሬታ ሲያቀርብ ግን የተለየ ነገር አላደረጉም።

መሸፋፈን፣ ማለባበስ፣ የመደባበቅ ፖለቲካ ከዚህ አድርሷቸዋል። 2007 እና 2008 መጀመርያ አካባቢ በተቃዋሚ የግንቦት 7ን ያህል አማራው ላይ ድጋፍ የነበረው ድርጅት የነበር አይመስለኝም። በ2008 ዓም፣ በዛ ክፉ ወቅት እንኳ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ፖሊሶች በግልፅ ይናገሩ ነበር። ያ አመት ግን መተዛዘቢያም ሆነ። ዛሬ ላይ ወጣቱ ጥላቻ ያዘ።

ይህ ጥላቻ ዝም ብሎ አይመጣም። በዛ መከራ ወቅት አምኖት አልተገኘም። ተሳስተሃል ሲባል አላስተካከለም። ዛሬም ገበሬው መሳርያ እንዲያወርድ የገዥዎች መጠቀሚያ በመሆን ላይ ነው። ይህ ሁሉ ስህተት ሲፈጠር አይተው እንዳላዩ ያለፈቱት ውጤቱን እያዩት ነው። ምክርን በቅንነት ያልሰሙ፣ መሬት ላይ ያለውን እውነት ስንናገር አሜሪካና አውሮፓ ሆነው "እውነታውን እናውቀዋለን" ያሉት ውጤቱን አዩት!

አሁንም ቢጠይቁ ጥሩ ነው! ለምን በወጣቱ ዘንድ ተጠላን? ለምን ከሰርን? እንዴትስ ብንሆን ይሻላል? ብለው ቢጠይቂ መልካም ነበር። ስህተትን መሸፈን፣ ስህተትን ማለባበስ ተለምዷል። ስህተትም ማመን አይታወቅም! ውጤቱ ይህ ሆነ!

እስኪ አሁንም ለምን ብላችሁ ጠይቁ!